# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT** — **جبهة تحرير اورومو**

Gaafa: 16/12/2015
Date: تاريخ

Lakk.: 18/stm - abo/2015
No.: رقم

## የወያኔ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያወጀውን ጦርነት በተመለከተ
## ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር የተሰጠ መግለጫ

ላለፉት 25ዓመታት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ጦርነት በማወጅ ሲገድልና ሲያስር የነበረው የወያኔ ኣናሳ ቡድን መንግስት ታህሳስ 15 ቀን 2015ዓም ለሁለተኛ ጊዜ ኣዋጁን በማደስ የኦሮሞ ህዝብ በሰላማዊ መንገድ እያካሄደ ያለውን ተቃውሞ ለማፈን የጦር ሃይሉ የፈለገውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስልጣን ሰጥቶታል። ይህ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የታወጀው ይህ የጦርነት ኣዋጅ ኣዲስ ባይሆንም ከቀድሞዎቹ በበለጠ የንጹሃን ዜጎችን እልቂት የሚያስከትል መሆኑ ኣያጠራጥርም።

በህዝቦች ጫንቃ ላይ በመውጣት ሲጨቁንና ሲዘርፍ የኖረው ይህ መንግስት የገጠመውን ተቃውሞ ሁሉ በሃይል ለመፍታት የሚያደርገው ጥረት እድሜውን ከማሳጠር በስተቀር መፍትሄ ኣያስገኝለትም። ስለሆነም በህዝባችን ላይ በታወጀው ጦርነት ለሚደርሰው እልቂት ተጠያቂው የወያኔ መንግስትና በዝምታ እየተመለከተ ያለው የኣለም ማህበረሰብ መሆኑን ኣነግ ከወዲሁ ያስገነዝባል።

የኦሮሞ ህዝብ ይህ ኣሸባሪ መንግስት ያወጀበትን ጦርነት በተቻለው መንገድ ሁሉ ከማክሸፍ በስተቀር ሌላ ኣማራጭ የለውም። ይህንን የጠላት ዘመቻ መቀልበስ ደግሞ መብቱ ነው። ስለሆነም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ይህንን ለመጋፈጥ ከዚህ በታች ያለውን ጥሪ ያስተላልፋል።

**1. በተለያዩ ጊዜያት ወታደራዊ ስልጠና ወስዳችሁ በህዝቡ ውስጥ ለምትገኙ የኦሮሞ ተወላጆች፥**
በህዝባችሁ ላይ የታወጀውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ በማክሸፍ የኦሮሞን ህዝብ ከእልቂት ለመታደግና ህዝባችሁን ለመከላከል በየመንደሩ እንድትደራጁ

**2. ትጥቅ ላላችሁ የኦሮሞ ዜጎች:**
በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተከፈተው ዘመቻ እናንተንም ያካትታል። ስለሆነም በግል ባላችሁ መሳሪያ ህዝባችሁን ከእልቂት ተከላከሉ። የችግር ቀን ደራሽ ወገን መሆናችሁን በተግባር ለማሳየት ከህዝባችሁ ጎን ኣትለዩ። ለዚህም ስልጠና ያላቸውን ማስታጠቁ የናንተ ግዴታ መሆኑንም እናሳስባለን።

**3. በውጪ ሃገራት ለምትገኙ የኦሮሞ ዜጎች:**
ዛሬ ህዝባችን መብቱን ለማስከበር በሰላማዊ መንገድ እያቀረበ ላለው ጥያቄ እየተሰጠው ያለው ምላሽ የሃይልና የጥይት መልስ ሆኗል። እየተካሄደ ባለው ኣመጽ ህጻናት ሳይቀሩ መስዋዕትነት እየከፈሉ ናቸው። በመሆኑም በተቻለላችሁ መንገድ ሁሉ የባዕድ ጭቆና ኣንገሽግሾት **ጭቆና ይብቃ!** በማለት ፍልሚያ እያካሄደ ካለው ህዝባችን ጎን ተሰለፉ። ከህዝቡ መካከል ስልጠና ኖሯቸው ህዝባቸውን ለመታደግ የሚደራጁትን በገንዘብ ደግፏቸው።

**4. በኦሮሚያ ውስጥ ለምትኖሩ የተጨቋኝ ብሄሮች ተወላጆች:**
ጠላት የኦሮሞን ህዝብ እንቅስቃሴ ለማክሰምና ለማፈን የተለያዩ ደባዎችን እየፈጸመ መሆኑ ከናነተ የተሰወረ ኣይደለም። የሃሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት በኦሮሞ ላይ እንድትነሳሱ በማድረግ እድሜውን ለማራዘም ይከጅላል። የኦሮሞ ህዝብ መብት መከበር የየትኛውንም ዜጋ መብት ኣይጋፋም። ስለሆነም ይህንን የጋራ ጠላት በጋራ መጋፈጥ ላለፉት 25ዓመታት ኣብረን የተጎነጨነውን መራር ጭቆና የሚያስወግድ መሆኑን በማወቅ የሚጠበቅባችሁን ድርሻ ኣበርክቱ። **በጠላት ኣንታለልም!** በማለት የወንድሞቻችሁ ኣጋር መሆናችሁን ኣሳዩ።

**5. በፋሽስቱ ስርዓት ስራዊት፣ ፖሊስና ልዩ ሃይል ውስጥ ለምትገኙ የተጨቋኝ ህዝቦች ተወላጆች በሙሉ:**
የኦሮሞ ህዝብ እያካሄደ ያለው የሙብትና የሃገር ባለቤትነት ትግል በሁሉም ተጨቋኝ ህዝቦች ላይ ለተዘረጋው የጭቆና ስርዓት ፍጻሜ ማበጀትን ያለመ እንጂ በህዝቦች ላይ የሚያደርሰው አንዳችም ጉዳት የለም። ስለሆነም በጠላት ፕሮፓጋንዳ ተታልላችሁ የኦሮሞን ህዝብ እንደጠላት አትዩት። በኦሮሞ ህዝብ ላይ የምታደርሱትን ግድያ፣ እስራትና ድብደባ በአስቸኳይ እንድታቆሙ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጥሪውን ያስተላልፍላችኋል። እየፈጸማችሁት ላለው ለዚህ ግድያ ነገ እያንዳንዳችሁ ተጠያቂ እንደምትሆኑ እናሳስባለን።

**6. ለመላው የአለም ማህበረሰብ:**
በወያኔ በምትመራው ኢትዮጵያ ውስጥ የተዘረጋው ስርዓት የህዝቦችን ፍላጎት የማያሟላ፣ የዲሞክራሲ ሙብትን የማያከብር፣ በህዝቦች ነጻነት ላይ እንቅፋት የሆነ፣ የህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን ሙብትን የማያከብር እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት በሚወስደው እርምጃ ሲያሳይ እንደነበርና እያሳየ እንዳለ ግልጽ ነው። ለዚህም በህዝቦች ላይ በተለይም ደግሞ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ሲወስድ የነበረው የጭካኔና ጠላታዊ እርምጃ ቀዳሚው ማስረጃ ነው። ዛሬ ይህ ሁኔታ ይብሱን አስከፊ ሆኖ ወደ ዘር ማጥፋት እርምጃ ተሸጋግሯል። ውሳኔው የተላለፈበት ህዝብ ደግሞ እራሱን ከእልቂት ለማትረፍ የተከፈተበትን ጦርነት መመከት የግድ ይላል።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው ሁኔታ በጊዜ መፍትሄ ካልተበጀለት በሩዋንዳ የተፈጸመውን ወደሚመስል ዘግናኝ እልቂት መሸጋገሩ የማይቀር ይሆናል። ስለሆነም ይህን መሰሉን እልቂት ማስቀረት በዲሞክራሲና በሰላም የሚያምኑ ወገኖች ግዴታና ሃላፊነት ነው። በተለይም ደግሞ የተባበሩን መንግስታት ድርጅት(UN)ግዴታ መሆኑን አጥብቀን እናሳስባለን።

የአለም ማህበረሰብ ይህንን ተገንዝቦ አሸባሪው የወያኔ መንግስት ከድርጊቱ እንዲገታና በሰላማዊ መንገድ ጥያቄውን ያቀረበው ህዝብ ሙብት እንዲከበር በማድረጉ ረገድ አስፈላጊውንና ተግባራዊ ጫና እንዲያደርግ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ይጠይቃል። ይህንን ባለማድረግ ወያኔ በህዝቦች ላይ በሚወስደው እርምጃ ለሚደርሰው እልቂት ከታሪክ ተጠያቂነት የማይወጣ መሆኑንም ያሳስባል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**
**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**
**ታህሳስ 16, 2015**